**<u>በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ የሚካሄድ ብሄራዊ ምክክር የማስጀመሪያ መርሀ-ግብር</u>**

**<u>መድረክ መክፈቻ ንግግር</u>**

- **የተከበሩ አቶ ደመቀ መኮንን - የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣**
- **የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር - የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣**
- **የተከበሩ አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣**
- **ክቡራን ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች እና ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣**
- **የተከበራችሁ የክልል መስተዳድር አፈ-ጉባኤዎች፣ ፕሬዚደንቶች፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች፣ የፍትህ ቢሮ ሃላፊዎች፣ ፖሊስ ኮሚሽነሮች፣**
- **ክቡራን አምባሳደሮች እና የአለማቀፍ ድርጅቶች ተወካይ ሀላፊዎች፣**
- **የተከበራቹህ ተጋባዥ እንግዶች፣**
- **ክቡራትና ክቡራን፣**

ሁላችንም እንደምንረዳው - ሁሉም በድህረ-ግጭት የፖለቲካ አውድ ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦች - ላለፉባቸው ውጣ ውረዶች፣ ዝንፈቶች፣ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ኢ-ፍትህዊነቶች ስር-ነቀል መፍትሄ ማበጀት - ከሚጠበቁባቸው ወሳኝ ተግባራት አንዱ እና ዋናው ነው።

በርግጥም በሽግግር ሂደት ላይ ያለ ማህበረሰብ - ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ ሲወጣ ወይም ለመውጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚያጋጥመው አንዱ እና አይነተኛው ፈተና - በግጭቶቹ፣ በጦርነት ወይም ጨቋኝ በነበረው ሥርዓት ለተፈፀሙ ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ አለመግባባቶች እና ሌሎች በደሎች ተገቢ መፍትሄ የሚሰጥበትን መንገድ መፈለግ፣ መዘርጋት፣ እንዲሁም ማህበረሰቡ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዳይመለስ ለማድረግ የሚያስችል ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ፣ መረጋጋት እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት ነው።

ይህ አይነቱን ታላቅ ግብ ለማሳካት - የተለመደው አካሄድ እና ዘዴ በቂ እና ተገቢ ባለመሆኑ ምክንያት - በበርካታ በሽግግር አውድ ውስጥ ባለፉ አገራት - በተለያየ መልክ የሚገለጽ የሽግግር ፍትህ ስርአት እና ሂደት ተግባራዊ ሲደረግ ማየት የተለመደ ነው።

በአጠቃላይ አገላለጽ - የሽግግር ፍትህ ስርአት - አንድ ማህበረሰብ ላለፈበት ከባድ፣ መጠነ-ሰፊ እና ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ በደሎች እና ኢ-ፍትህዊነቶች - ተገቢ ምላሽ የሚሰጥበት አሰራር ወይም ሂደት ነው። የሽግግር ፍትህ ሂደቶች - ከእርስ በርስ ጦርነት፣ ግጭት እና ጭቆና በመውጣት የፖለቲካና የዲሞክራሲ ሥርዓት ሽግግር ለማድረግ በሞከሩ ሀገራት በተለያየ መንገድ የተሞከሩበት እና ዘለቄታዊ ሰላም፣ እርቅ እና ፍትህ በማስፈን ከፍተኛ አስተዋፅዎ ያደረጉበት አጋጣሚ ብዙ ነው።

በዚህ ረገድ - በዓለም አቀፍ ደረጃ - የተባበሩት መንግስታት ድርጅት - በሽግግር ላይ የሚገኙ ሀገራትና ማህበረሰቦች - ተጠያቂነትን፣ ፍትህን እና እርቅን ባማከለ መንገድ የሚያከናውኑት የሽግግር ፍትህ ሂደት ሊደገፍ የሚገባው ስለመሆኑ አጽንኦት ሰጥቶ ሲገልጽ እና በተለያዩ ሀገራት የተሞከሩ የሽግግር ፍትህ ሂደቶችንም ሲያግዝ ቆይቷል።

በአህጉራችን አፍሪካ ደረጃም - በ2011 ዓ.ም በመዲናችን አዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ማዕቀፍ - በሂደቱ የሚያልፉ ሀገራት - አሳታፊ በሆነ የምክክር ሂደት የሚተገብሯቸውን የተለያዩ የፖሊሲ እርምጃዎች እና ተቋማዊ አሠራሮችን በዝርዝር አመልክቷል። አገራትም የሰነዱን ገዢ ሀሳቦች ስራ ላይ በማዋል - ያለፉ ጥሰቶችን እና ክፍፍሎች ለማከም እና ለማስወገድ፣ እንዲሁም ለደኅንነት፣ ለዴሞክራሲ፣ እና ለማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ግንባታ ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ከማድረግ አንጻር - የሽግግር ፍትህ አሰራርን በቁርጠኝነት ተግባራዊ እንዲያደርጉ የፖሊሲ ማዕቀፉ ይጠይቃል።

- **ክቡራትና ክቡራን፣**

የሽግግር ፍትህ አሰራር መሰረታዊ ግብ ባለፉ ጊዜያት ለተፈጸሙ በደሎች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ መስጠት - በዚህም ዘላቂ ሰላም፣ ፍትህ፣ ተጠያቂነት እና እርቅን ማስፈን ነው። በሌላ አነጋገር የሽግግር ፍትህ አሰራር እርስ-በርሱ የተጠላለፈ፣ በአንድ ጊዜ ወደ ኋላም እና ወደፊትም የሚመለከት ዓላማ ያለው ሂደት ነው። በውስጡም በተለይ ለተጎጂዎች፣ በአጠቃላይ ደግሞ በማህበረሰብ ደረጃ - በቀደሙ ጊዜያት ለደረሱ ጥፋቶች ሁሉን-አቀፍ ምላሽ መስጠት፣ አጥፊዎችን መቅጣት፣ እውነትን ማረጋገጥ፣ የተጎዱትን መጠገን ወይም በማካካሻ ስርአት ማቀፍ፣ ለተጎጂዎች ተገቢ ክብር መስጠት፣ ተመሳሳይ በደሎች እንዳይከሰቱ መከላከልን፣ እንዲሁም ብሄራዊ መግባባቶችን ማሳለጥን የሚመለከቱ ዝርዝር አላማዎችን አካቶ የያዘ ነው።

ከዚህ አንጻር - ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ - በርካታ አገራት - የሽግግር ፍትህ አላባዎች እና ስልቶችን በመጠቀም - ላለፉ ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተጠያቂነትን በማስፈን - በሽግግር ፍትህ ስልት ፍትህን ለማረጋገጥ ሞክረዋል። በተጨማሪም - ሀገራት የሽግግር ፍትህ ስልት ማእቀፍን - እውነትን ለማጣራት እና ይፋ ለማውጣት፣ እርቅን የማስፈን፣ የማካካሻ እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ እንዲሁም የወሳኝ ተቋማትን ለውጥ ለማሳለጥ ሲጠቀሙበት በስፋት ይታያል።

እነዚህ የሽግግር ፍትህ ስልቶች እርስ-በርስ የሚተካኩ ሳይሆን - አንዱ ሌላውን የሚደግፍ እና የሚመጋገቡ በመሆናቸው - በሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት እንደየነባራዊ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ አውዳቸው እና የችግሮቻቸው አይነት ወይም ጥልቀት - የተመረጡ ወይም ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን ተግባራዊ ሲያደርጉ ቆይተዋል። እንዲያደርጉም ይጠበቃል።

- **የተከበራችሁ ተጋባዥ እንግዶች፣ ክቡራትና ክቡራን፣**

ቀደም ባሉ ጊዜያት - ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ በምትገኝበት አውድ ውስጥ የነበሩ ሌሎች ሀገራት - ከገቡበት ችግር ለመውጣት የተለያዩ ስልቶችን በተቀናጀ እና በተጠና መልኩ ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን እንደተጠበቀ ሆኖ - ሀገራችንም በተለያዩ ጊዜያት በተለያየ ደረጃ በሚገለፁ የሽግግር ሂደቶች ውስጥ ማለፏንም መገንዘብ ተገቢ

ነው። ሆኖም እነዚህ ሀገራዊ ሑደቶች በቂ እና በተሟላ መልኩ የሽግግር ፍትህ ሂደትን ያሰቡ፣ ያደራጁ ወይም የተገበሩ አልነበሩም። በርግጥም ከታሪካችን እንደምንረዳው - በሀገራችን የመንግስታት ለውጥ በተከሰተባቸው የቅርብ ጊዜያት ሁሉ - ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በደሎች እና ጭቆናዎችን መንስኤ፣ ምንነት፣ አይነት እና የጉዳት መጠን በበቂ መንገድ በማጣራት - እውነትን ለማውጣት እና ለጉዳት እውቅና ለመስጠት፣ ተጠያቂነትን ለመመስረት፣ እንዲሁም በይቅርታ እና እርቅ ላይ የተመሰረተ የተሟላ ስርአት ለመመስረት የተሄደበት መንገድ ወይም የተከወነው ስራ እጅግ በጣም ውስን ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ሲባል ግን - በሀገራችን ባለፉት ዘመናት ለተፈጸሙ በደሎች፣ ጥሰቶች ወይም ቁርሾዎች መፍትሄ ከመስጠት አንጻር - ምንም አይነት ሙከራዎች ወይም ልምምዶች አልነበሩም ማለት አይደለም። ለማሳያም ያህል በ2010 ዓ.ም. በሀገራችን የተፈጠረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ - መንግስት ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና በደሎችን በእውነት፣ በእርቅ እና በፍትህ ላይ ተመስርቶ ለመፍታት እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መንገዱን ለማመቻቸት በሚል - አንዳንድ የሽግግር ፍትህ እርምጃዎችን መውሰዱ ይታወሳል። ከነዚህም ውስጥ - መንግስት በህዝቡ ላይ ለደረሱ በደሎች እንደመንግስት በይፋ ይቅርታ መጠየቁ፣ የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሙ፣ እና ለሽግግር ፍትህ ሂደት አስተዋፅዎ የሚያደርጉ የህግ እና የተቋማት ማሻሻያ ስራዎችን ማከናወኑ በተለይ የሚጠቀሱ ስራዎች ናቸው።

- **ክፍተትና ክፍተት፡**

እንደዚህም ሆኖ - የተወሰዱት ውስን እርምጃዎች - ከአለማቀፍ መርሆች እና ምርጥ ተመክሮዎች ቅመራ ጋር በሚጣጣም መልኩ - አካታች እና አሳታፊ በሆነ ሂደት ካለመዘጋጀታቸውም በላይ - የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተሟላ መልኩ ባካተተ እና ተቀናጅቶ በሚተገበር የፖሊሲ አቅጣጫ የተመሩ አልነበሩም። አንዱ እርምጃ ከሌላው እርምጃ ጋር ያለው መስተጋብር በግልፅ የተለየ፣ የታሰበበት ወይም የተደነገገም አልነበረም። በዚህም ምክንያት - የተወሰዱት እርምጃዎች ወይም የተከወኑት ስራዎች የየራሳቸው በጎ አስተዋጽኦ ቢኖራቸውም - ሁሉን-አቀፍ ከሆነ የሽግግር ፍትህ አሰራር አንጻር ሲመዘኑ - ሰፊ ጉድለት ስለነበረባቸው የታለመላቸውን አላማ ማሳካት አልቻሉም።

ስለሆነም በተሟላ እና በተቀናጀ መልኩ የሚዘረጋ፣ ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ፣ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ በሌሎች ሀገራት እና በሀገራችን ከነበሩ ልምምዶች ትምህርት የሚወስድ፣ እንዲሁም በሀገራችን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድ ላይ መሰረት የሚያደርግ የሽግግር ፍትህ ሂደትን - አሳታፊና አካታች በሆነ ሂደት በመቀመር እና በማዘጋጀት - የሀገራችን የሽግግር ፍትህ ስርአት በግልፅ የፖሊሲ ማእቀፍ እንዲመራ ማድረግ - እጅግ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ እና አስገዳጅ መሆኑን ሀገራዊ አውዱ በግልጽ ያመላክታል።

በዚሁ አግባብም - በቀጣይ ለሚዘጋጀው ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ - አማራጭ ሀሳቦችን ለውይይት ለማቅረብ እና ግብአት ለመሰብሰብ እንዲቻል “የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ማዕቀፍ አማራጮች” የመነሻ ሰነድ በባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ቀደም ሲል ይፋ መደረጉ ይታወሳል።

በዛሬው እለትም - በሚቀጥሉት ሳምንታት በሀገር-አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው የግብዓት ማሰባሰቢያ የውይይት እና ምክክር መድረኮች መርሃ-ግብር የመክፈቻ እና ማስጀመሪያ ስነ-ስርአት በይፋ መጀመሩ ታላቅ አገራዊ ፍጻሜ ነው።

በመሆኑም ሁላችሁም ባለድርሻ አካላት - ለዚህ ሂደት መሳካት የሚጠበቅባችሁን አስተዋጽኦ እና እገዛ እንድታድርጉ የአደራ መልክቴን እያስተላለፍኩ - ቆይታችሁ በውጤታማ ውይይት እና ምክክር የታጀበ እንዲሆን መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ።

**አመሰግናለሁ!!!**